# ክህደት እየተፈጸመ ነዉ!

*ከ33 ዓመታት በፊት የደርግን ስርዓት በመቃወም ትጥቅ ትግልን እንደ ብቸኛ አማራጭ በመዉሰድ ጫካ ከገቡ ጥቂት የሕወሃት አባላት አንዱ የሆኑት አቶ ስዬ አብርሃ በዉጊያና በጦር አዛዥነት በተሳተፉባቸው ታላላቅ አውደ ዉጊያዎች በበርካታ የሕወሃት አባላት ዘንድ በጀግንነታቸዉ ይወደዳሉ።*

*በዚህ ተግባራቸዉ የተበሳጨዉ ደርግ ወላጅ አባታቸዉን በግፍ ገድሎ፣ ወንድማቸዉን ረሽኖ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን አጠናቆ ሥራ ሊጀምር በዝግጅት ላይ የነበረ ታናሽ ወንድማቸዉን በማሰር ከባድ የምራልና የስነልቦና ስብራት ቢያደርስባቸዉም፤ አቶ ስዬ ግን በዚህ አልተንበረከኩም። በርካታ የጦርነት እቅዶችን በመንደፍና የሚታወቁት አቶ ስዬ በተለይ ግንቦት 20/1983 ኢሕአዴግ አዲስ አበባ ሲገባ በአራቱ አቅጣጫዎች የቀመሩት ወታደራዊ ንድፍ ተጠቃሽ ነዉ።*

*ኢሕአዴግ ግንቦት 20/1993 ዓ.ም መላዉ አገሪቱን ከተቆጣጠረ በኋላ በተቋቋመዉ የሽግግር መንግስት፣ የአገሪቱ የመከላከያ ሚኒስትር ሆነዉ ያገለገሉት አቶ ስዬ «ደርግ በእኔና ቤተሰቤ ላይ የፈጸመዉ ግፍ አሁንም በኢሕአዴግ እየተደገመ ነዉ» ይላሉ። አክለዉም «ተግንቦት 20 አስረኛ አመት ሲከበር እኔን ጨምሮ ስምንት የቤተሰቤ አባላት ለእሥር ተዳረግን። ዘንድሮ 17ኛ አመቱ ሲከበር ደግሞ ወንድሜ አሰፋ አብርሃም የእኔ ወንድም በመሆኑ ብቻ የአመክሮ መብቱ ተነፍጎ የፍትህ ያለህ እያለ ነዉ» ይላሉ። (ለአቶ አሰፋ አብርሃ የስዬ ወንድም በመሆናቸዉ ብቻ በደርግ አገዛዝ ለረጅም ጊዜ በግፍ ታስረዉ ግንቦት 20/1983 መለቀቃቸዉ ይታወሳል) ስለ ግንቦት 20 በመንግስት ብዙ እየተባለ ባለበት ሁኔታ «ማን ይናገር የነበረ፤ ማን ያርዳ የቀበረ» ነዉና ስለ ራሳቸዉ ብዙ መናገር የማይፈልጉት አቶ ስዬ በጦር ትዝታዎቻቸዉ ዙሪያ ከአውራምባ ታይምስ ጋር ያካሄዱት ልዩ ቃለ ምልልስ እነሆ፡-*

**ግንቦት 20 እንደ ብሄራዊ በዓል በየአመቱ መከበሩ ፋይዳዉ ምንድን ነዉ ይላሉ ?**

ግንቦት 20 የደርግ ፋሺስታዊና አምባገነናዊ ስርዓትን በመቃወም ኢትዮጵያዉያን «እምቢ አንገዛም፣ ግፍና አፈናዉ ይብቃ» ብለዉ ለረጅም አመታት እየወደቁና እየተነሱ እየሞቱና እየቆሰሉ፣ ረጅሙ የፖለቲካ ተጋድሎ መቋጫና ማሳረጊያ ያገኘበት ዕለት ነዉ። ግንቦት 20 የኢሕአዴግ ብቻ አይደለም። እነኛ የተሰዉት፣የተገደሉት፣ የቆሰሉትና የታሰሩት፣ የችግርና መከራ ገፈት እማሽ የሆኑት ዜጎችንም ይመለከታል። ለዘመናት ፍትሕ የተጠሙ ኢትዮጵያዉያን ድልም ነዉ ግንቦት 20። በእርግጥ ትግሉን ኢሕአዴግ አስተባብሮ መርቷል። እነኚህ ግን ኢትዮጵያዉያን በመሆናቸዉ የኢትዮጵያዉያን ገድል መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ኢሕአዴግ «በብቸኝነት የእኔ ሰማዕታት ናቸዉ» ብሎ የግሉ የሚያደርግበት አንዳች ምክንያት የለም። ትግሉ የመላዉ ኢትዮጵያዉያን ትግል ነዉ። በዓሉም የመላዉ ኢትዮጵያዊያን ገድል ዉጤት ነዉ።

**አንዳንድ ወገኖች ግን «ግንቦት 20 አምባገነኖች የተቀያየሩበት ቀን ነዉ፤ ካኪ የለበሰ አምባገነን ሲፍ በለበሰ አምባገነን የተተካበት ዕለት ነዉ» ያላሉ። የእርስዎስ አስተያየት ምንድ ነዉ ?**

መንግስቱ ኃይለማሪያም እኮ ካኪዉን አዉልቆ ከራቫት ያስር ነበር። በእርግጥ ይለያያሉ። የሚያመሳስላቸዉም ነገር አለ። የመንግስቱ ኃይለማሪያም አፋኝ አገዛዝ የመጣዉ በቀዝቃዛ ጦርነት ዘመን ነዉ። ያ ዘመን ደግሞ እንደምናዉቀዉ አለም በሁለት ጎራ ተከፋፍላ በአንድ በኩል ምዕራባዉያን ካፒታሊስቶች፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሶቭየት የምትመራዉ የምስራቅ ሶሻሊስቶች ካምፕ ፍጥጫ ላይ የነበሩበት ወቅት ነበር። በዚህ ወቅት አምባገነኖች ለአንድ ወገን አድረዉ እንደልባቸዉ የሚፈነጩበት ጊዜ ነዉ የነበረዉ። እነ መንግስቱ፣ ሞቡቱ፣ ሴሴሴኮ እና አዉጉስቶ ፒኖቼን የመሳሰሉ አዉሬዎች በሚደግፏቸዉ አይዞህ ባዮች ጉያ ተከልለዉ ይኖሩ ነበር። ዛሬ በአለማችን ያለዉ ነባራዊ ሁኔታ ግን ይህንን አይፈቅድም። ስለ ሰብዓዊ መብት መከበር፣ ስለ ነጻ ምርጫ፣ ስለ መደራጀት፣ ስለ ነጻ ገበያና ወ.ዘ.ተ. የሚዘመርበት ወቅት ላይ እንገኛለን። «በአንዱ ዘንድ ተጠግቼና በአንዱ ጉያ ላይ ተወሽቄ የፈለኩትን አደርጋለሁ» ማለት የማይታሰብ ነዉ።

የአሁኑ ዘመን አምባገነኖች የእነ መንግስቱ እና የእነ ሞቡቱ ሴሴሴኮ አይነት መልክ ያላቸዉ አይደሉም። አሁን ያሉት አምባገነኖች ስለ ሰብዓዊ መብት እየሰበኩ ሰብዓዊ መብትን የሚረግጡ፣ ስለ ዲሞክራሲና የዜጎች ነጻነት እየዘመሩ በተግባር ግን ተቃራኒዉን የሚፈጽሙ፣ ስለ ነጻ ምርጫ፣ ነጻ ፕሬስ፣ ስለ መደራጀት እየተናገሩ ይህንኑ የሚያፍኑ ናቸዉ።

አሁን ባለዉ የአለማችን ሁኔታ የበለጠ የሚያዋጣዉ ላይ ላዩ ጥሩ ቅብ ተቀብቶ ዉስጡ ለዉስጥ ግን ሌላ ሆኖ እያስመሰሉ መኖር ነዉ። ይህ እንግዲህ የሚያመሳስላቸዉና የሚያለያያቸዉ መሰረታዊ ነገር ነዉ።

አመጣጣቸዉም እንደዚሁ የተለያየ ነዉ። በእኔ እምነት የመንግስቱ ኃይለማሪያም አገዛዝ በኢትዮያዉያን አብዮት ላይ ተረማምዶ የመጣ፣ በርሱ ላይ ያመጸና በማቃብሩ ላይ የቆመ አፋኝ አገዛዝ ነዉ። ኢሕአዴግ የታገለዉ ይህንን በአብዮቱ መቃብር ላይ ቆሞ፣ ሰብዓዊ መብትና የብሄር ብሄረሰቦችን የእኩልነት መብት የረገጠዉን የደርግ ስርዓት ነዉ። ይህ ሁለንታናዊ አፈና «አሁን ተቆልፎ ከሚገኝበት አሳዛኝ ሁኔታ መዉጣት አለበት» የሚል የተስፋ ጭላንጭል ይዞ ነዉ የመጣዉ። በሂደት ግን የተገባዉ ቃል ተሸሮ ክህደት እየተፈጸመ ነዉ። ከዚህ

ሆኔታ አንጻር ሁለቱም ወደ ፖለቲካ ስልጣን የመጡበት ሁነታ ልዩነት አለዉ። ያም ሆኖ ግን አሁን ሥልጣን ላይ ያለዉ የኢሕአዴግ መንግስት የተለያዩ የማስመሰያ ቴክኒኮች ስለተጠቀመ ብቻ «አፋኝ አምባገነን» ከመባል አይተርፍም።

**ቅድም ስለ ሁለቱም ካምፖች (የምዕራብ ካፒታሊስቶችና ሶቪየት መራሹ የምስራቅ ሶሻሊስት) ሲገልጹ ዛሬ ላይ ያሉ አምባገነኖች እንደነ ሞቡትና መንግስቱ የሚሸሸጉበት እድል እንደሌለ ደምድመዋል። ቻይና ግን በአሁኑ ወቅት የአፍሪካ አምባገነኖች ቀጣይ መሸሸጊያ ዋሻ ልትሆን እንደምትችል ትንታኔ የሚሰጡ ወገኖች አሉ። እርስዎ ይህንን እንዴት ያዩታል?**

ሶቪየት ህብረት ካልተረፈች ቻይናስ ይቀርላታል ወይ ? የሚል ጥያቄ መመለስ አለበት። ወዴት ነዉ እየጋደለ ያለዉ ? አሁን ባለንበት ወቅት ሶሻሊዝም ብትለዉ ሌላ ስምም ብትሰጠዉ ከነጻነት ዉጭ ሌላ መንገድ ያለ አይመስለኝም። እነ ቻይና ይህንን ማዕበል ተቋቁመዉ በዚህ መልኩ እስከመሸቼ ይዘልቃሉ ? ራሳቸዉን እያስተካከሉ በሂደት አለም ወደ ተቀበለዉ አስተሳሰብ የሚሀዱበት እድልስ ቢፈጠር ?

ጥያቄዉ ሲሻሊዝምን የመገንባት ያለመንገንባት ጉዳይ አይደለም። የዜጎች ነጻነት፣ የሰዎች ሰብዓዊ መብት፣ የሰዎች የመተንፈስ መብት አፍኖና ቆልፎ መኖር የሚቻለዉ እስከመቼ ነዉ ? ይህ መመለስ ያለበት ጥያቄ ይመስለኛል። በእኔ እምነት ለሶቪየት ካምፕ መፈራረስ ዋነኛዉ ምክንያት ይህ ነዉ።

**ከ30 አመታት በፊት ፓርቲያችሁ ትጥቅ ትግልን እንደ ብቸኛ አማራጭ በመያዙ ጫካ ስትገቡ የአጭርና የረጅም ጊዜ አላማ ሊኖራችሁ እንደሚችል ግልጽ ነዉ። ለዚህም አላማ ብዙዎች መስዋዕት ሆነዋል። አላማዉ ምን ነበር ? ያ አላማስ ግቡን መቷል ብለዉ ያምናሉ ?**

የትግሉ አለማ የነበረዉ የደርግ ስርዓትን ማስወገድ ነዉ። የደርግን ስርዓት ማስወገድ የተፈለገበት ምክንያት ስርዓቱ ለዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት፣ ለብሄር በሄረሰቦች እኩልነት መከበር እንቅፋት ስለሆነ ነዉ። በ 1966 ዓ.ም. በነበረዉ የሕዝብ እንቅስቃሴ የተነሱ የመብት ጥያቄዎችን ዳር ለማድረስ ደርግን መጣል አንድ ዓላማ ቢሆንም መጨረሻዉ ግን እርሱ ብቻ አልነበረም። ከእርሱ ባሻገር ደርግ የደፈጠጣቸዉ ሰብዓዊና ዲሞራሲያዊ መብቶችን ማስከበር ነዉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ በሃገሪቱ የተረጋጋ ዲሞራክራሲያዊ ስርዓት እንዲሰፍንና የአገሪቷ መሰረታዊ ችግሮች ላይ ትኩረት አድረጎ አስቀያሚዉን የአገራችን የተመጽዋችነት ገጽታ ለመቀየር ነበር።

እንግዲህ ከዚህ አኳያ ሲታይ ደርግንና አስቀያሚዉን ገጽታዉን በመጣል በኩል የትግሉ አላማ ተሳኳቷል። ደርግ እንዲወድቅ የተፈለገበት ፖለቲካዊ ምክንያቶችም ተመልሰዋል ወይ ? የተባለዉ በእርግጥ የመመለስ ተስፋ ነበር። በሂደት ግን በጣም በሚያሳዝን ሆኔታ እየጨለመና እየጠፋ አሁን ያለንበት አፋኝ የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ላይ የደረስንበት ሁኔታ ነዉ ያለዉ።

ለምንድን ነዉ እንደዚህ የሆነዉ ? ሕወሃት/ኢሕአዴግ እንደ ሽምቅ ተዋጊ መጀመሪያ ያደረገዉ በትጥቅ ትግል መፋለም ነዉ። ይህን ለማድረግ ደግሞ ሰራዊት ማደራጀትና ያንን ትግል በስኬት መምራትን ይጠይቃል። ይህንን ካላሳኩ ከዚያ ባሻገር ያሉ ነገሮች ላይ አይደረስም። ስለዚህ ይህንን ነገር ማሳካት የግድ ይላል። ይህ በመሆኑ ደግሞ የትጥቅ ትግሉ ወሳኝ ቦታ እንዲኖረዉ አድርጎታል። ሕወሃት የፖለቲካ ድርጅት ነዉ። እንደ ፖለቲካ ድርጅት ፕሮግራም አለዉ። ሕገ ደንብ አለዉ። በሌላ በኩል ግን ሕወሃት/ኢሕአዴግ ሰራዊት ነዉ። የደርግን ጦር አሸንፎ ለመጣል የተደራጀ የስራዊት ተቋም ነዉ። ሁለት ሆኖ ደግሞ መሄድ አይችልም። ምክንያቱም እዉነተኛ የፖለቲካ ፓርቲ ለመሆን ሰፊ የዉስጥ ዲሞክራቲክ አደረጃጀትን ይጠይቃል። የሲቮክ ሕይወት ይፈልጋል። ስለዚህ ሕዝቡ እራሱ በፖለቲካዉ እየተደራጀ መብቱን የሚያስጠብቅበት አካሄድ ሊኖረዉ ይገባል።

ወደ ትጥቅ ትግልና ሰራዊት ማደራጀት ስትመጣ ጠንካራ ወታደራዊ ዲሲፕሊንና የእዝ ስርዓትን ይጠይቃል። እነዚህ ሁለቱ ተቃራኒ ነገሮች ናቸዉ። እዛ በነበርንበት ሁኔታ ሁለቱን አስታርቆ መሄድ አይቻልም። የያኔዉን አሁን ተመልሼ ሳየዉ የትጥቅ ትግሉ በጣም አነስተኛ በሆነ አቅም በሚገባ የተሳካ ነበር ከትንሽ ኃይል ተነስቶ ያንን ያህል ግዙፍ ሰራዊት ሊያሸንፍ የሚችል ሰራዊት መገንባት፣ ይህንን ሊያሳካ የሚችል ስትራቴጂ እና ስልት ቀይሶ ዳር ማድረስ ከባድ ሥራ ነበር። ግን ተደርጓል።

ይህንን ለማሳካት ተብሎ እራሱን ያደራጀ ድርጅት ይኸዉ አምጥቼዋለሁ ብሎ አምጭና ሰጪ ሆኖ እንጂ ሕዝቡ እራሱ የእኔ ብሎ የሚጠይቅበት የራሱ መዋቅር የራሱ ነጻ አደረጃጀቶች ገንብቶ ያመጣዉ አይደለም። እንዲህ አይነት ነጻ አደረጃጀት እንዲኖሩ ኢህአዴግ ፈቃደኛ አልነበረም። መልሶ ሊወስድ የሚችልበት ወይም ወደ ሳጥኑ የሚከትበት ሁኔታ ነበር የነበረዉ፤ አሁንም የሆነዉ ይሄ ነዉ።

**ለሰማዕታት መዘከሪያ በተለያዩ ቦታዎች ሃዉልቶች ይሰራሉ። የመታሰቢያ ፕሮግራሞችም ይዘጋጃሉ። እነኚህ ሃዉልቶችና የመታሰቢያ ፕሮግራሞች ኢሕአዴግ የሰማዕታቱን ራእይና አላማ መጠበቁን ያሳያል ?**

ቅድም እንዳልኩህ እነኚህ ሰማዕታት የአንድ ድርጅት ሰማዕታት አይደሉም። የኢሕአዴግ የግል ንብረትም አይደሉም። ኢትዮጵያ ዉስጥ ፍትህ እንዲመጣ፣ ዲሞክራሲ እንዲገነባ ራሳቸዉን አሳልፈዉ የሰጡና በክብር የወደቁ ኢትዮጵያዉያን ሰማዕታት ናቸዉ። ይህ ትግል የኢትዮጵያ ታሪክ አካል ነዉ። የኢሕአዴግ ሰማዕታት ተብለዉ አንሰዉ እንዲታዩ አልፈልግም። ታሪካቸዉን በዚህ አኳኋን ጠባብ በሆነ ሲዘከር መስማት ዉለታቸዉን ማሳነስ ነዉ። ይህ የሁላችንም ኢትዮጵያዉያን ገድል ነዉ። ልዩነት ሊኖረን ይችል

ይሆናል። ሁሉንም የኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦች ተወላጆችን አላሳተፉ ይሆናል። ግን እነዚያ የተሳተፉት ደግሞ ኢትዮጵያዉያን መሆናቸዉን መዘንጋት የለብንም።

በትግራይ የሰማዕታት ሃዉልት ተሰርቷል። በበህር ዳርና በአዳማም እንደዚሁ ተሰርቷል። መታሰቢያነቱ ጥሩ ነዉ። በተለያየ አጋጣሚ የሀገር ባለዉለታ ለሆኑ ኢትዮጵያዉያን ብዙ ግፍ ለደረሰባቸዉ ዜጎች ማስታወሻ መስራት ተገቢ ነዉ።፡የካቲት 12 ቀን በጣሊያን ፋሺስታዊ አገዛዝ ለተጨፈጨፉት ኢትዮጵያዉያን ሃዉልት ተሰርቷል። የአቡነ ጴጥሮስን ሃዉልትም ተጠቃሽና ተገቢ መታሰቢያ ነዉ። በመስቀል አደባባይም በተመሳሳይ ሁኔታ በቀይ ሽብር ለተጨፈጨፉት ሰማእታት መታሰቢያ እየተሰራ ነዉ። ምክንያቱም እነኚህ የቀይ ሽብር ሰለባ ወገኖቻችን የኢሕአፓ አባላት የሆኑ አሉበት፤ የሕወሃት አባላትም አሉበት። የመኢሶንም አባላት ይገኙበታል። የማንም አባል ያልሆኑም ነበሩ። ግን ደግሞ ሁሉም ኢትዮጵያዉያን ናቸዉ። ለነዚህ ሰማዕታት ሃዉልት ማቆሙ ተገቢ ነዉ።፡መነሻቸዉ ምንም ይሁን ምን ከየት ድርጅት ይምጡ እኔ እንደ ዜጋ ለነኝህ ሰማእታት ትልቅ አክብሮት አለኝ። ወደ ሕወሃት/ኢሕአዴግ ስንመለስ እኔ አመራር በነበርኩበት ጊዜ የእኔን አመራር ተቀብለዉ የእኔ ቃል አምነዉ ፈንጅ እየረገጡ ለተሰዉ ሰማዕታት ያለኝን አክብሮት ዘመን አይሽረዉም።

እንደግለሰብም አባቴና ወንድሜ በግፍ የተገደሉብኝ ሰዉ ነኝ። ስለዚህ ግፍና በደል የተፈራረቁበት፣ ፍትህ ከተነፈገ ቤተሰብ መሃል የወጣሁ ነኝ። ለነዚህ ሰማዕታት ሊደረግላቸዉ የሚገባ ዉለታ እምነበረድ ጠርቦ ማቆም ብቻ ነዉ ወይ ? ብለን መጠየቅ አለብን። እነዚህ ወገኖቻችን ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ባለመኖሩና በነጻ ዳኝነት እጦት ጥፋታቸዉ ሳይታወቅ፣ የመከራከር እድል ሳያገኙ ፍትህ ተነፍገዉ እንደ አዉሬ በየጢሻዉ የተወረወሩ ወገኖቻችን ናቸዉ። አብዛኞቹ ኋላ ላይ መረጃ ተሰብስቦ ነዉ አጽማቸዉ ከየጢሻዉ ተቆፍሮ የወጣዉ። **የእኔ አባት ለምሳሌ የመቀሌ ሕዝብ ነዉ አጥንቱን አዉጥቶ የሰጠኝ።** ለእነዚህ ሰማዕታት « እግዚአብሄር ይቀበላችሁ። በመንግስተ ሰማያት ኑሩልን» ብለን ከልባችን ከማለት ሌላ ማድረግ ያለብን ያለ አይመስለኝም።

ታዲያ መደረግ ያለበት ምንድ ነዉ ?

መደረግ ያለበትማ በእነርሱ ላይ የደረሰዉ ችግር እንዳይደገም ዋስታና ሊሆን የሚችል ስርዓት ሲገነባ፣ ነጻ ዳኝነት ኖሮ ከእንግዲህ ወዲያ ማንም ኢትዮጵያዊ ጥፋቱ ሳይታወቅ ፣ ሳከራከር፣ በነጻ ዳኝነት በህግና ከህግ አኳያ ብቻ የሚፈርድ ዳኛ ሳይኖር እንዳይታሰር ሰብዓዊ መብቱ እንዳይጣስ፤ ሕይወቱን እንዳያጣ ማድረግ የሚያስችል ስርዓት ማቋቋም ነዉ። የፈለገዉ አይነት ርዝመትና ወርድ ያለዉ ኃዉልት ቢገነባ የሚያማምሩ ቃላት ያሉበት ኃዉልት ቢሰራ፣ ይህንን አይተካዉም። ይህ ደግሞ አሁን የለም። ይህንን በየቦታዉ እስካልተከልን ድረስ «የሰማዕታትን አደራ አክብረናል፤ ሰማዕታትን ዘክረናል። እነሱ ያለፉበት መንገድ ከቶ አይደገምም» ብለን አፋችንን ሞልተን ለመናገር ምንም አይነት የሞራል ብቃት አይኖረንም።

የሚያሳዝነዉ ደግም እራሱ ኢሕአዴግ «የሰማዕታት አደራ አለብኝ» እያለ በሰማዕታት ስም እየማለ ይህ እንዳይፈጸም እንቅፋት መሆኑና የሰማዕታት ፍላጎት እዉን እንዳይሆን እራሱ ሰማዕታቱ የተሰዉለት ድርጅት ግንባር ቀደም ጋሬጣ መሆኑ ነዉ።

**ግንቦት 20 17ኛ አመት ላይ ደርሰናል። ወደ ኋላ ልመልስዎትና ግንቦት 20/1983 የት ነበሩ? ሁኔታዉንስ እንዴት ያስታዉሱታል?**

እዛ ማዘዣ ጣቢያዉ ዋሻ ዉስጥ ነበር የነበርኩት። በቴሌቭዥን አይታችሁት ከሆነ የኢሕአዴግ ኮማንድ ፓስት (ማዕከላዊ እዝ) ተምቤን ሃገረ ሰላም በሚገኝ ዋሻ ዉስጥ ነዉ የነበረዉ። እኔ በዕለቱ እዛ ዉስጥ ነዉ የነበርኩት። ከእኔ ጋር ተወልደ ወልደማሪያም ነበር። እሱ የማዕከላዊ ኮማንድ አባል ነበር። አቶ ታምራት ለአይኔም እዛ ዉስጥ አብሮኝ ነበር። የድርጅቱ (የኢሕአዴግ_ ምክትል ሊቀመንበርና የማዕከላዊ ኮማንድ አባል ነበር።

እና ግንቦት ግንቦት 20/1983 ሶስታችን እዚያች ዋሻ ዉስጥ ነበርን። ይህን የመጨረሻ ዘመቻ ስናስተባብር የነበርነዉ እኛ ሶስታችን ነበርን። አቶ መለስ ደግም ለንደን ነበር የነበረዉ። በዋለልኝ የተሰየመዉ ዘመቻ ማለትም ደቡብ ወሎ ፣ ደሴ፣ የመንዝ አካባቢ በሙሉ በስኬት ተጠቃሎ በምዕራብ በአምቦ ግንባር የነበረዉን ኃይላችንም ወደ አዲስ አበባ ተጠግቶ በሰሜን ሸዋ በኩልም ሰንዳፋ ድረስ ቀርቦ ነበር፤ በቆላ የሄደዉ ደብረዘይት ደርሶ እንደዉም ባለሥልጣናት በአዉሮፕላን ሊወጡ ነዉ የሚል ነገር ሰምተን ስለነበር «ምንም አይነት አይሮፕላን ወደ አዲስ አበባ እንዳይገባና እንዳይወጣ» የሚል መመሪያ በሬዲዮ እያስተላለፍን ነበር።

በዚህ መሰረት ወደ አዲስ አበባ ለመግባት በመጨረሻ ምዕራፍ ላይ እያለን ከደርግ ባለሥልጣናት ጋር ለመደራደር ቀደም ሲል ወደ ለንደን የተላከዉ አቶ መለስ ድርድሩ መክሸፉን ገለጸልኝ። በዚህ ሁኔታ ላይ አዲስ አበባ ሳንገባ ለቀናት መቆየት አደጋ ስላለዉ ሰራዊቱ አዲስ አበባ መግባት እንዳለበት ከመለስ ጋር ተስማማን።

ከመለስ ጋር የስልክ ዉይይት እንደጨረስኩኝ አምባሳደር ተወልደ ገብሩ፣ ካቶ መለስ ጋር እዚያዉ ለንደን ስለነበረ «ተወልደን አቅርብልኝ» ብዬ መለስን ተሰናበትኩት። እሱ ከለንደን ወደ አዲስ አበባ በስልክ ይገናኝ ስለነበር። አዲስ አበባ ምን አለ ? ብዬ ስጠይቀዉ «ፍርሃት አለ። ሕዝቡ በየቤተክርስቲያኑ ገብቶ ጸሎት ላይ ነዉ ያለዉ» አለኝ። የሰራዊቱ አባላት ጠመንጃቸዉን እየሸጡ፣ ልብሳቸዉን እየቀየሩ ሕብረተሰቡን እየተቀላቀሉ ነዉ። የዝርፊያ አደጋ አለ። ከዚያም አልፎ እሥር ቤት የነበሩትን በተለይም የታጋይ ቤተሰብ የሆኑትን ገድለዋቸዋል ይባላል» አለኝ።

እንግዲህ በዚህ ወቅት ወንድሜ አሰፋ አብርሃ እሥር ቤት ነበር። ደርግ የእኔ ወንድም በመሆኑ ስምንት አመት ዳኛ የሚባል ሳያይ እዛ ታስሮ ነበር። በርግጥ እርሱ ብቻ አይደለም። የሕወሃት፣ የኦነግ አባላት የሆኑ እና ሌሎች ብዙ ኢትዮጵያዉያን እዛ ታስረዉ ነበር።

እንግዲህ የታጋይ በተሰቦች ተገደሉ ከተባለ የመጀመሪያዉ ኢላማ ሊሆኑ ከሚችሉት አንዱ የእኔ ወንድም ነበር። የሰማሁትን ዋጥ አድርጌ ደህና ሁን ተባብለን ከተወልደ ጋር ተለያየን። የሬዲዮ ቴሌግራፍ መጻፊያ ደብተር እንዲመጣልኝ አዝዤ የሬዲዮ ተእዛዝ ለመጻፍ ተዘጋጅቼ ቁጭ አልኩኝ። ስልኩን ከዘጋሁት በኋላ ዝም ነበር ያልኩት።

እዚያ ዋሻ ዉስጥ አብሮኝ የነበረዉ ተወልደ ወልደማሪያም ዉጭ ቆይቶ ሲመጣ በድርድሩ እና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ከነመለስ ጋር በስልክ ያወራነዉን ነገርኩት። እንግዲህ ከተወልደ ጋር ሳወራ ባልተለመደ ሁኔታ ቀዝቀዝ ብዬ ነበር መሰለኝ ፣ ተወልደ የሆነ ነገር እንደሆንኩኝ ሳይጠረጥር አልቀረምና ምን እንደሆንኩኝ አጥብቆ ጠየቀኝ። ልደብቀዉ ብሞክርም ተጭኖ ጠየቀኝ። ሰለ ወንድሜ የሰማሁትን ነገርኩት። «እኔ ዛሬ አላለቅስም። የማለቅስበት ቀንም አይደለም» ብዬ ከራሴ ጋር ቃል ስለገባሁ እንባ እንኳን አልወጣኝም። «ብዙ ጓደኞቻችን ተሰዉተዉ ትግሉ እዚህ ደርሶ ባለበት ሁኔታ ሌላ ከባድ መስዋዕትነት የሚጠይቅ የዉጊያ ትዕዛዝ ለመጻፍ በተዘጋጀሁበት ሁኔታ ወንድሜ ሞተ ብሎ ማልቀስ ተገቢ አይደለም» በማለት ከራሴ ጋር ተማክሬ ሃዘኔን ዉጬ ብቀመጥም ተወልደ ግን በቤተሰቤ የደረሰዉን ስቆቃ ያዉቅ ነበርና እንደነገርኩት ወዲያዉኑ እንባዉ መዉረድ ጀመረ። «ተወልደ የምናለቅስበት ቀን አይደለም» ብዬ አረጋጋሁትና ወደ ስራችን ገባን።

**ከዚያ በኋላስ ?**

ከዚያ በኋላ ሰራዊታችን ወደ አዲስ አበባ እንዴት መግባት እንዳለበት ትእዛዝ የመስጠት ስራ ተጀመረ። ከተለያዩ አቅጣጫ የመጡ የሰራዊቱ ክፍሎች ማን የትኛዉን ቀጠና መቆጣጠር እንዳለበት አስቀድሜ አስቤበት ስለነበር እያንዳንዱ ግንባር ከየት እስከ የት መሆን እንዳለበት ያለዉን ወሰን ማን መያዝ እንዳለበት ሰፊ ትእዛዝ ሰጥቼ መልእክቱ ተላለፈ። ሁላችንም እንደምናዉቀዉ ወሳኙ ሥራ ጦርነቱ ከአዲስ አበባ ዉጭ እንዲያልቅ ነበር የታሰበዉ። ስጋቶች ቢኖሩንም የመንግስቱ ኃይለማሪያም መሸሽና የባልስላጣናቱ መፈረካከስ በከተማዉ የተደራጀ ተቃዉሞ እንደማይገጥመን በቂ ምልክቶች ነበሩ። እንደ ተመኘነዉ ሆኖ ከባድ እልቂት አልደረሰም። በዚህ ደግም በጣም የሚያስደስተኝ ነገር ቢኖር ብዙ ጉዳት ሳይደርስ አዲስ አበባን መቆጣጠር መቻላችን ነበር።ግንቦት 20 በእኛ በኩል ደስታዉ ወደር የለዉም።

***ወንድምዎ በሕየወት መኖሩና አለመኖሩን ታዲያ እንዴት አረጋገጡ ?***

የወንድሜ ነገር ተወልደ ዓጋሜ (አምባሳደር ተወልደ) ከሰጠኝ መረጃ ዉጭ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ አላዉቅም ነበር። በትግሉ ዉስጥ አብሮኝ የነበረ አንድ ሌላ ወንድም አለኝ:: ሻለቃ ወልደ ሥላሴ ይባላል። ሻለቃ ወልደ ሥላሴ ከጻድቃን ወልደ ትንሳይ ስር ነዉ የነበረዉ። ሰራዊቱ አዲስ አበባ ከመግባቱ በፊት አስቀድሞ መረጃ ለማሰባሰብ አንድ ጠንከር ያለ ልዩ ኃይል አዲስ አበባ እንዲገባ ተደርጎ ነበር። ሻለቃ ወልደሥላሴ ከነዚህ ዉስጥ አንዱ ነበር። ስለ አሰፋ ግን ያወቀ አይመስለኝም። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን እኔ እኔም ምንም የማዉቀዉ ነገር አልነበረም። ምክንያቱም ቀጥታ ግንኙነቴ ከአለቃዉ ጋር ስለነበረ የተሰጠዉም ሥራም ዘመቻ ነክ ስለሆነ ማለት ነዉ።

ግንቦት 21/1983 ዓም. ይመስለኛል « ኃየሎም ወደ ሬዲዮ ቅረብ ይልሃል» ብለዉ የእኔ የሬዲዮ ሰራተኛ ጠሩኝ። አብዛኛዉን ጊዜ ሚስጥር እንዳይወጣ በሚል በቃል ብዙ አንነጋገርም። «ስለዚህ ቴሌግራም ነዉ የምንጠቀመዉ። ለምን በሬዲዮ ሊያናግረኝ ፈለገ?» ብዬ ሳወጣና ሳወርድ የሬዲዮ ሰራተኞቹ ደግሞ «አሁን ቅረብ ብሎሃል» አሉኝ። ካለሁበት 100-150 ሜትር ርቆ ነዉ ሬዲዮዉ የሚገኘዉና በጥዲፊያ ወደ እዛ ሄድኩኝ።

እኔ የመሰለኝ ከዚያ በፊት ግንቦት ሃያ፣ ሳሞራ የኑስ አራተኛ ክፍለጦር አካባቢ የተወሰኑ ጄኔራሎች የተወሰነ ኃይል ይዘዉ አንድ 20 የሚሆኑ ታንኮች ይዘዉ እጅ አንሰጥም ብለዉ ለመዋጋት እየተንገራገሩ ነዉ» ብሎ በሬዲዮ አነጋግሮኝ ነበር። ለሁላችንም ስጋት የነበረዉ በመሃል አዲስ አበባ በመድፍ እና በታንክ ዉጊያ ቢከፈት ብዙ አደጋ ይደርሳልና ነገሩ ትኩረት የሚፈልግ ስለሆነ እንዴት እናድርግ ብሎ ለመነጋገር ነበር ከሳሞራ ጋር በሬዲዮ በፍጥነት እንድቀርብ ጠይቄ የነበረዉ። በዚህ ዙሪያ ያዉ ተመካክረን እንዳሰብነዉ በሰላም አለቀልን።

«እና ዛሬ ግንቦት 21 ምን አሳሳቢና አስቸጋሪ ነገር ተፈጥሮ ነዉ ኃየሎም በጥዲፊያ እንድቀርብ የፈለከዉ» ብዬ በፍጥነት ሄድኩኝ። በሬዲዮ ተገናኝተን ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ እንግዳ አለህ ብሎ ሲያገናኘኝ ለካ ያ እንግዳ ወንድሜ አሰፋ ኗሯል። ከእስር ቤት ወጥቶ፣ አጠያይቆ፣ ተሾላልኮ፣ « ኃየሎም ያለበት ቦታ ዉሰዱኝ» ብሎ በርሱ በኩል ወንድሜ በሕይወት መኖሩን ከራሱ ድምጽ ስሰማ ድሉ የተሟላ ሆነልኝ።

***መቼ ነበር እርስዎ ከሃገረ ሰላም ዋሻ ወደ አዲስ አበባ የመጡት ?***

በሚሊተሪ አሰራር ማዕከላዊ እዝ በአንዴ አይለቅም። ግንኙነትህን አቋርጠህ፣ ነቅለህ ፣ አጥፍተህ አትሄድም። ስለዚህ ሰራዊቱ አዲስ አበባ እንደገባ እኛ ሶስታችን (እኔ ተወልደ ወልደማሪያምና ታምራት ለአይኔ) ተመካክረን አንድ በአንድ መሄድ እንዳለብን ተስማማን። በመጀመሪያ አቶ ታምራት እንዲሄድና እነ ጻድቃን፣ አለምሰገድ፣ ሳሞራና ኃየሎምን እንዲያስተባበርና አዲስ አበባ ገብቶ ሰራዊቱንም ሌሎችን ስራዎችን እንዲሰራ ወሰንን። በዚህ መሰረት በመጀመሪያ እርሱ እንዲሄድ ተደረገ። እርሱ

ገባሁ ሲል ተወልደ ተንቀሳቀሰ። ተወልደ አዲስ አበባ መግብቱ ከተረጋገጠ በኋላ ጠባቂዎቹን ደህና ሁኑ ብዬ ተምቤን ሀገረ ሰላም ዋሻ የነበረዉን ማዕከላዊ እዝ በመልቀቅ እኔ የመጨረሻዉ ሰዉ ሆንኩኝ። በ 21 ወይንም 22 ማት ይመስለኛል አዲስ አበባ የገባሁት። ትዝ የሚለኝ አቶ መለስ ከለንደን ወደ ካርቱም መጥቶ ከካርቱም አዲስ አበባ ሲገባ ከእኔ ጋር እኩል በአንድ ቀን መግባታችንን ነዉ።

**ከወንድምዎት ጋር የተገናኙበትንስ ቀን ያስታወሱታል ?**

ወዲያዉኑ አዲስ አበባ ገብቼ እዩ ቤልዩ ቤተ መንግስት አጠገብ ባለዉ ጌስት ሃዉስ እኔና መለስ ተገናኝተን ቁጭ ብለን እየተጫወትን ሳለ ነበር ወንድሜ አሰፋ የመጣዉ። ሲመጣ ሁለታችን (እኔና መለስ) ተቀበልነዉ። በዚያን ጊዜ አቶ መለስ ደስ ብሎት ሻምፓኝ ከፍቶ ነበር። «ወንድማችን እንኳን በሰላም ከኛ ጋር ቀላቀለህ፤ አሮጊቷዋም እንኳን ይህን አዩ» ነበር ያለዉ። ምክንያቱም ደርግ በቤተሰቤ ላይ ምን ያህል ሰቆቃ እንደፈጸመ ያዉቃል።

**ግንቦት 20 እስረኛ አመት ሲከበር በ 1993 ኢ.ም የነበረዉ ሁኔታስ እንዴት ያስታዉሱታል ?**

(ሳቅ) ግንቦት 20/1993 ዓ.ም. በመጥፎ ሁኔታ ነዉ የማስታዉሰዉ። እንደሚታወቀዉ ግንቦት 20 ብሄራዊ በዓል ነበር። በማግስቱ 21 ቀን እኔና ሌሎች የቤተሰቤ አባላት በሙሉ ታፍሰን እሥር ቤት የገባንበት ቀን ነዉ። እኔ በጸረ ደርግ ትግል የተሳተፍኩት ከሶስት ወንድሞቼ ጋር ነዉ። አሰፋም ቢሆን ቅድም እንደነገርኩ ግንቦት 1983 ነበር ከእሥር ቤት የወጣዉ ። ዘበኞቹ ትተዋቸዉ ስለሄዱ እዚያዉ ቀርተዉ የነበሩ እሥረኞች በሩን እራሳቸዉ ከፍተዉ ነበር የወጡት። መንግስቱ ኃይለማሪያም አልፈታቸዉም። ጄኔራል ተስፋዬም አልፈታቸዉም። ዘበኞቹ፣ ኢሕአዴግ አዲስ አበባ መቃረቡን ሲያዉቁ ትተዉ ስለሸሹ ነበር እስረኞቹ ከእሥር ቤት የወጡት።

ግንቦት 20 ማግስት (በ21/09/1993) አሳዛኙ አጋጣሚ ተፈጠረ። ስምንት የቤተሰብ አባላት ታፍሰን እሥር ቤት የገባንበት ቀን ነዉ። ሶስቱ በትግሉ ወቅት ከኔ ጋራ የታገሉ ወንድሞቼ፣ እህቴንና ታናሽ ወንድሜን (ምህረተ አብ) ከነባለቤቴ ለእሥር የተዳረግንበት ጊዜ ነበር። ከዚያ በኋላ ብዙ መከራና ችግር አይተን ብዙዎቻችን ተፈተናል። አሁንም ግን ወንድሜ አሰፋ አብርሃ አልተፈታም። አሰፋ በመንግስቱ ኃይለማሪያም ጊዜ ከስምንት አመት በላይ ታስሯል። በመለስ ዜናዊ ደግሞ ሰባተኛ አመቱን ግንቦት 21/2000 አስቆጥሯል። እድል ይሁን እንጃ .. ከዩኒቨርሲቲ ከተመረቀ ወዲህ ሳይታሰር በነጻነት የቆየዉ ከ 1983-1993 ዓ.ም. ያለዉን ጊዜ አሥር አመት ብቻ እንጂ ሌሎችን ጊዚያት በእሥር ነዉ ያሳለፈዉ።

ሙስና ብለዉ ከሰሱት። ይህ ሳያንሳቸዉ ምንም ጥፋት ሳይሰራ ዘጠኝ አመት ፈርደንብሃል አሉት። እንግዲህ በኢትዮጵያ ሕግ አንድ ሰዉ የፍርዱን ሁለት ሶስተኛ ከፈጸመ በአምክሮ ይፈታል ነዉ የሚለዉ። እኔ ሐማሌ 4 ስፈታ ስድስት አመት ከአርባ ቀን ነበር የታሰርነዉ። እንደ ሕጉ ከሆነ አሰፋ ከኔ ጋር መፈታት ነበረበት። ግን አመክሮ ተከልክሎ እስከ አሁን ድረስ እሥር ቤት ነዉ የሚገኘዉ። ከአሰፋ ጋር በአንድ ፋይል ነዉ ተከሰዉ ስምንት አመት የተፈረደባቸዉ አቶ በሻህ አዝብቴ የሚባሉ ሰዉ አመክሮ ተሰጧቸዋል። እርሱ በአንድ ፋይል ብቻ ሳይሆን፣ በአንድ ክስ ከርሳቸዉ ጋር አብሮ የተፈረደበት ሆኖ እያለ እርሱ እስካሁን ድረስ አመክሮ ተነፍጎታል። በቀይ ሽብር ግፍ ላይ የተሳተፉ ሰዎች፣ በሃዉዜን ጭፍጨፋ (ድብደባ) ላይ የተሳተፉ ፓይለቶች፣ ተፈርዶባቸዉ ሁለት ሶስተኛ የእስር ጊዚያቸዉን ሲፈጽሙ አመክሮ ተሰጥቷቸዋል። በእኔ እምነት ይህ ተገቢ ነዉ እላለሁ። አሰፋ ለሌሎች የተሰጠዉ መብት አሁንም ድረስ ተነፍጎት በእሥር ይገኛል።

**ግንቦት 20/2000ን እንዴት አዩት** ?

ትራጄዲ ነዉ። የኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ትራጄዲ ነዉ። አብረን ትግል ጀምረን፣ ብዙዎች በትግሉ ሂደት ወድቀዋል። እስከ ትላንትናዉ የትጥቅ ትግል ዉስጥ በአመራር ደረጃ የነበርን ሰዎች የት እንዳለን ታዉቃላችሁ ? አሁን እዚያ ተንቤን ባለዉ የኢሕአዴግ ማዕከላዊ እዝ ዋሻ ዉስጥ የነበርነዉ ሶስት ሰዎች አሁን በድርጅቱ ዉስጥ የለንም። እንግዲህ ደርጎችም በዛ ብለዉ ነዉ የጀመሩት። እነ ጄኔራል አምን አንዶም፣ ጄኔራል ተፈሪ ባንቲ፣ ኮሎኔል አጥናፉ ... ወ.ዘ.ተ. ሆነዉ ነበር የጀመሩት። በኋላ ግን መንግስቱ ኃይለማሪያም ብቻዉን ነዉ የቀረዉ።

አመሰግናለሁ አቶ ስዬ